# ጥንት ነጭ በተደጋጋሚ ሽንፈቱን ተከናንቦና ተዋርዶ የወጣባት አገር ኢትዮጵያ,,,,,

ዛሬ ብቃት በሌላቸው መሪዎቿ ተዋርዳ በነጮቹ በእነአሜሪካ ትዕዛዝና አድራጊ ፈጣሪነት፣ቅኝ ተገዥነታችን ግልፅ እየሆነ መጥቷል።
በአንድ አገር ውሰጥ "በራስ ላይ መተማመን ወይም "Self reliance"ካለ ማንም አገር ጣልቃ የመግባት ዕድል የለውም።
እነአፄ ምኒልክ የ17ኛውን አንቀፅ ተከትሎ ኢጣሊያ ያደረገችውን ጣልቃ ገብነት አጥብቀው በመቃወማቸው፣
ኢጣሊያ ጦር ሲያዘምት፣በራስ ላይ በመተማመን ጦር አዝምተው የነጭን ጣልቃ ገብነት በአጭር ቀጭተዋል።
እንግሊዝ፣ኢጣሊያና ፈረንሳይ ሶማሊያን በመሣሠሉት አካባቢዎች አገርን ቆራርጠው ቅኝ ይገዙ ሥለነበርና አንዱ ሌላውን ለማሰወገድ ይጥሩ ሥለነበር፣በአፄ ምኒልክ የአድዋ ጦርነት፣ኢጣሊያንን እንድንወጋበት ፣ ፈረንሳይ መድፍ ሠጥቶናል።

በድጋሚ ኢጣሊያ ሲወረን 5ዓመት ሙሉ ሥንዋጋው፣የእንግሊዙ ጄኔራል ዊንጌት ሱዳን-ካርቱም ውሰጥ የኢትዮጵያን ወታደሮች እያሠለጠነ፣ ይልክልን ነበር።
እንግሊዝ ይህንን መሠል ሥራዎቹን ወይም ውለታዎቹን መግቢያ በማድረግ፣አፄ ኃይለሰላሴ ወደአገር ለመመለስ በመንገድ ላይ እንዳሉ፣እንግሊዝ ቀድሞ አዲሰ አበባ ገብቶ ባንዲራውን በማውጣት "እኔ ነኝ ነፃ አውጫችሁ " የሚል ዕደምታ ያለው ጣልቃ ገብነት ለማሳዬት ሲሞክር፣ንጉሱ ደርሰው ለተደረገው ዕርዳታ ሞቅ ያለ ምሥጋና አቅርበው በበሰለ ዲፕሎማሲ፣የእንግሊዝን ጣልቃ ገብነት አሰቁመው፣ሸኝተዋል።
የዛሬዎቹ ጉዶች ግን አገሪቱን በእነአሜሪካ ጣልቃ ገብነት ብቻ ሳይሆን አሜሪካ በአጠቃላይ ነጮች የሚወሰኑባት አገር አድርገው ሸጠዋታል።

መሪ የተባሉትን እንደፈለጉ እያሽከረከሩ፣ከዚህ ውጡ ከዚህ ግቡ እያሉ፣በራሳችን ራሳችን እንዳንወሰን፣ውሳኔው የአሜሪካ ሆኗል። የዘመኑ ቅኝ ተገዥ (Neocolonialism)ለመሆን በቅተናል።
Self reliance ወይም በራስ ላይ መተማመን ሞቶ ተቀብሯል። ከእነአገሪቱ ማንነታችንንና ክብራችን አሳልፈን ሠጥተናል።
ይህ የሚሰማውና የሚቆጨው ተነሰቶ የነበረውን አይበገሬነት መመለሰ ካልቻለ፣በቁመና ሞተናል።
ልብ ያለን ልብ እንበል!!!